# በሙኒክና አካባቢዉ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ደጋፊ ግብረሐይል

## Kinijit Support Group Munich/ Germany

### *የአቋም መግለጫ*

***ለሚመራው የፖለቲካ ድረጅት መመሪያና ደንብ የማይገዛ መሪ ወደፊት ለምንመኘው ሀገራዊ ሕገመንግሥት ይገዛል ማለት ዘበት ነው!***

በምንደግፈው የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ የተከሰተው ችግር ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈታል ብለን ሰንጠብቅ ከአመራር ጉድለትና ከአያያዝ ስህተት አቅጣጫውን ስቶ አሉታዊ ውጤት በማምጣቱ እጅግ በጣም ያሳዘነን ጉዳይ ሆኗል:: መታገል የሚገባቸውን የጋራ ባላንጣ ወደጎን በመተዉ ለግል ጥቅምና ዝና የሀገርና የወገንን አደራ መዘንጋትን የሚያክል ጥፋትና ክህደት ሊኖር አይችልም ! ስለሆነም እንዲህ ዓይነቱን አስነዋሪ ተግባር የሚፈጽሙና ትግሉን ወደኋላ የሚጎትቱ ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን መደገፍ ቀርቶ ዳር ቆመን ለማየት የሚያስችለን ህሊና ሊኖረን አይገባም ::

የድጋፍ ድርጅታችን ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲን ለመደገፍ የፈለገው የፓርቲውን የአመራር ቦታ የያዙ ግለሰቦች ተክለ ሰውነት ስቦት ሳይሆን ለድርጅቱ የተግባር መመሪያ እንዲሆን የነደፉት ማኒፌስቶና ለሕዝባችን የገቡት ቃልኪዳን ማቀርኮን ነው ::

እስካሁን ድረስ የፓርቲውን ራእይ እውን ለማድረግ በተደረገውና እየተደረገ ባለው ጥረት ምክንያት ብዙ ሕይወት አልፏዋል ፣ ለእስራትና ለስደትም ተዳርገዋል ግፉ ግን አሁንም አላበቃም :: ይህ በእንዲህ እያለ የወገንን ስቃይ ለማራዘም ከፓርቲው አመራር ውስጥ ለመመሪያና ደንብ የማይገዙ አመባገነኖች መከሰታቸው እጅግ በጣም አሰቆጥቶናል !

ስለሆነም የድጋፍ ድርጅታችን  ፌብሩአሪ 16.02.2008 ባካሄደዉ ጠቅላላ ጉባኤ ታህሳሰ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፓርቲው ሊቀመንበር በእንጂነር  ሃይሉ ሻውል የተወሰደውን እርምጃና ከዚያም በፊት ሆን ብለው በተከታታይ የፈጸሙትን ሰህተቶች አስመልክቶ በስፋት ከተወያየ በህዋላ የሚከተለውን አቋም ለመውሰድ ተገዷል :-

1. እንጂነር  ሃይሉ ሻውል በድርጅቱ ደንብ መሰረት ለአብላጫ ድምጽ ተገዠ መሆን ሲገባቸው መመሪያንና ደንብን እየጣሱ በምንደግፈው ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ውሰጥ አመባገነንነት እንዲሰፍን መጥፎ አርአያ በመሆናቸው እጅግ አሳዝኖናል፣

2. ሊቀመንበሩ መመሪያንና ደንብን እየተላለፉ ከፓርቲው አመራር አካል እስከ ድጋፍ ድርጅቶች ኢ-ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያካህዱትን የሹም ሽር የማንቀበልና አጥብቀን የምንቃወም መሆናችንን ማስገንዘብ እንወዳለን ፣

3. በሊቀመንበሩ ሕገወጥ ደርጊት እየተመሩ የፓርቲውን ህልውና አደጋ ላይ ለመጣል የሚጥሩ ጥቂት የላእላይ ምክር ቤት አባላት ከአፍራሽ አድራጎታቸዉ እንዲቆጠቡ እያስገነዘብን ድርጊታቸዉን አጥብቀን እንቃወማለን፣

4. የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የላዕላይ ም/ቤት ታህሣሥ 20 ቀን 2000 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያስተላለፈው ውሳኔ መመሪያና ደንብን የተከተለና ተገቢ በመሆኑ እንደግፋለን

created using
BCL easyPDF
Printer Driver
Click here to purchase a license to remove this image

5. በዲያስፖራ ይካሄድ የነበረዉ ከፍተኛ ትግል የቅንጅት አመራሮች ከእስር ከተፈቱ በኋላ ግባችን እነሱን ማስፈታት ብቻ ይመስል ደብዛዉ መጥፋቱ በጣም ያሳሰበን በመሆኑ ከመሰል አቻ ድርጅቶች ጋር በመሆን ለአገርና ለወገን የሚደርገዉ የዲሞክራሲ ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል እናሳስባለን፣

6. የአገር ቤቱን ትግል ለማገዝ በዉጪዉ ዓለም በየአካባቢዉ በግል ፍላጎት የተቋቋሙ የድጋፍ ድርጅቶች ሀይላቸዉን አስተባብረዉ ዉጤት ያለዉ ተግባር ለማከናወን ይችሉ ዘንድ በእኩልነትና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ከአገር አንስቶ እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደርስ ዲሞክራሲያዊ የሆነ ድርጅታዊ የግንኙነት ሰንሰለት እንዲፈጠር አፋጣኝ እንቅስቃሴ እንዲደረግም ጥሪ እናደርጋለን ።

7. በአዉሮፓ አቀፍ ካሁን በፊት ተቋቋመ የሚባለዉ የአዉሮፓና የአፍሪካ ካዉንስል ከታች ወደላይ ዲሞክራሲያዊ የሆነ የአደረጃጀት መርህን ያልተከተለና ከየድጋፍ ድርጅቶች ዉክልናን ያላገኙ ተጠሪነትና ተጠያቂነት የሌላቸዉን ግለሰቦች ያካተተ በመሆኑ ትግሉን ከማጓተት በተጨማሪ ወገኑንና አገሩን በፍላጎቱ ለመርዳት የተሰባሰበዉን ህዝብ አንድነት እየናደና እየበተነ በመሆኑ ይህ የሁሉንም የድጋፍ ድርጅቶች ማንዴት የለለዉ ካዉንስል ተወግዶ ሁሉንም የድጋፍ ድርጁቶች ያካተተ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተዋቀረ ካዉንስል በሁሉም ተሳትፎ እንዲቋቋም እናሳስባለን።

በሙኒክና አካባቢው የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ደጋፊ ግበረሃይል
ጠቅላላ ጉባኤ
16.02.2008
ጀርመን (ሙኒክ)

created using
BCL easyPDF
Printer Driver
Click here to purchase a license to remove this image